
ምስባክ ዘፍልሰታ ጸም
ነሐሴ ፳፻፲፭ ዓ/ም

ምስባክ ዘፍልሰታ ጾም

ነሐሴ ፳፫ ቀን ዓ/ም

አስተዳላዊ ሀብተ ማርያም ገላው

መታሰቢያነቱ

ግእዝ ቋንቋን እዚህ ላደረሱልን እና እንደ መምህር ግዛቸው ደጀኑ ለትውልድ ለማስተላለፍ ለሚጥሩ ኹሉ ይኹን !!!

መክሥተ አርእስት

አርእስት ገጽ

መግቢያ 6

ዘነሐሴ ፩ 9

ዘነሐሴ ፪ 16

ዘነሐሴ ፫ 22

ዘነሐሴ ፬ 28

ዘነሐሴ ፭ 34

ዘነሐሴ ፮ 38

ዘነሐሴ ፯ 43

ዘነሐሴ ፰ 48

ዘነሐሴ ፱ 54

ዘነሐሴ ፲ 61

ዘነሐሴ ፲፩ 67

ዘነሐሴ ፲፪ 74

ዘነሐሴ ፲፫ 81
ዘነሐሴ ፲፬ 86
ዘነሐሴ ፲፭ 93
ዘነሐሴ ፲፮ 98

መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

የግእዝ ቋንቋ ለኢትዮጵያ መሠረቷ ፤ ዐምዷ እና ምሰሶዋ እንደኾነ በእኛ በልጆቿ ቀርቶ ኢትዮጵያን ከሩቅ ኾነው ታሪኳን የሚያውቁ ሰዎች የሚመሰክሩት ሐቅ ነው ።

ይህም ይታወቅ ዘንድ ሌሎች በግእዝ በተጻፉ ብራናዎቻችን ላይ ጥናት በማካሄድ በዘመናዊ መልኩ በመጠቀም ብዙ ነገር እንዳተረፉ ገሃድ የወጣ የታወቀ ነገር ነው ።

እኛ ደግሞ መረባችንን ለሰው አሳልፈን ሰጥተን ዓሣ የምንለምን ሰዎች ኾነናል ።

መረባችን ግእዝ እና በግእዝ የተጻፉ መጽሐፎቻችን ሲኾኑ ዓሣው ደግሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ይጠቀምባቸው ዘንድ የፈጠራቸው ፍጥረታት በሙሉ

ናቸው ። አባቶቻችን ለምስጢር ቅርብ ስለነበሩ ማንኛውንም ምስጢር በግእዝ ቋንቋ ቄልፈው ፤ ቋንቋውን ትተውልን ዐልፈዋል ።

የእኛ ድርሻ ግእዝን መማር እና ወደ ተግባር መቀየር ነው ።

ይህንን የተገነዘቡት መምህር ግዛቸው ደጀኑ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ዘመኑ ያፈራውን መገናኛ ብዙኃን በመጠቀም እና ለትምህርት ቀላል በኾነ እና ግልጽ በኾነ መንገድ ሙዳየ ግእዝ ቍጥር ፩ መጽሐፍን በመጻፍ ብዙ የግእዝ ቋንቋ ተማሪዎችን እያፈሩ ይገኛሉ ። ለወደፊቱም ግእዝ ቋንቋን ለኢትዮጵያውያን ለማስተማር ትልቅ ራእይ ሰንቀው እየሠሩ ይገኛሉ።

የፍልሰታ ጾምን ምክንያት በማድረግ በፍልሰታ ጾም የሚባሉ ምስባካትን የግእዝ ቋንቋ መማሪያ ይኾኑ ዘንድ በመምህር ግዛቸው ደጀኑ እና ከአንደኛ እስከ ዐሥራ አንደኛ ዙር ባስተማሯቸው ተማሪዎች ተዘጋጅቶ ቀርቧል ።

“በምስባካቱ ውስጡ ያሉ ቃላት ምን ማለት ናቸው ?” የሚለውን ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር ተማሪዎች የተማሩትን ይተገብሩበት ዘንድ የተወሰኑትን በምሳሌነት ሠርቶ በማሳየት ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ እንደሚከተለው ሠርተው እንዲያቀርቡ ያከፋፈሉ ሲሾን ተማሪዎችም በጥሩ ኹኔታ አዘጋጅተው አቅርበዋል ።

ይህንን ምስባክ ያዘጋጁት መምህር ግዛቸው ደጀኑ እና ከአንደኛ እስከ ዐሥራ አንደኛ ዙር የተማሩ ተማሪዎች ተውጣጥተው ሲሾን ስማቸው ከምስባኩ ግርጌ ተቀምጧል።

የግእዝ ቋንቋ ቋንቋ ብቻ ኣይደለም ዕውቀት፣ ጥበብ፣ ማስተዋልም ጭምር እንጂ !!!

ሀብተ ማርያም ገላው ከፀኛ ዙር

ነሐሴ ፩

ምስባክ ዘነሐሴ ፩ ።

▪ መዝ ፻፲፰፥ ፻፯ - ፻፷

ወእነግር ሰምዐከ በቅድመ ነገሥት ወኢይትሃፈር።

ወአነብብ ትእዛዘከ ዘአፍቀርኩ ጥቀ።

ወአነሥእ እደውየ ኀበ ትእዛዝከ ዘአፍቀርኩ።

▪ መዝ ፻፲፰ (፻፲፱) ፥ ፻፯-፻፷

በነገሥታት ፊት ምስክርኽን እናገራለኹ አላፍርምም፤

እጅግም በወደድኋቸው በትእዛዛትኽ ደስ ይለኛል።

እጆቼን ወደ ወደድኋቸው ወደ ትእዛዛትኽ ፡ አነሣለኹ፣

ትምህርታችንን በተግባር

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር የቃሎች አመጣጥ እንደሚከተለው ነው።

- **ወእነግር**
  - ነገረ ➳ ነገረ
  - ነገርኩ ➳ ነገርኾ
  - እነግር ➳ እነግራለኾ
  - እንግር ➳ እነግር ዘንድ
  - እንግር ➳ ልንገር
- **ሰምዐከ**
  - ሰምዐ ➳ ሰማ፣ አደመጠ፣ አስተዋለ

    ➳ መሰከረ፣ ምስክር ኾነ

- ስምዕ ➳ ምስክር፣ ምስክርነት
- ስምዕከ ➳ ምስክርኽ
- ስምዐከ ➳ ምስክርኽን (ተሳቢ)

- **በቅድመ**

- ቀደመ ➳ ቀደመ
- ቅድም ➳ ፊት፣ በፊት
- ነገሥት (መድበል ቅጽል) ከ ነግሠ
- በቅድመ ነገሥት ➳ በነገሥታት ፊት
- በ ➳ አገባብ፣ ፍቺው ➳ በቁም ቀሪ፣

  ሙያው ➳ ማድረጊያ

- **ወኢይትጎፈር**

- ጎፈረ ➳ ዐፈረ (ከራቍትነት የተነሣ)
- ተጎፍረ ፣ ተጎፈርኩ ➳ ፈራ፣ ተፈራ

- ይትጎፈር ፣ እትጎፈር ➳ እፈራለኹ
- ይትጎፈር ፣ እትጎፈር ➳ እፈራ ዘንድ
- ይትጎፈር ፣ እትጎፈር ➳ ልፍራ
- ኢይትጎፈር ➳ አላፍርም
- ወኢይትጎፈር ➳ አላፍርምም

- **ወአነብብ**

- አንበብኩ ➳ ተናገርኹ
- አነብብ ➳ እናገራለኹ
- አንብብ ➳ እናገር ዘንድ
- አንብብ ➳ ልናገር

- **ትእዛዘከ**

- ዐዘዘ ➳ ጸና፣ በረታ፣ ጠነከረ
- ዕዘዝ ➳ ጽናት፣ ብርታት፣ ጥንካሬ

- አዘዘ ➳ አዘዘ
- ትእዛዝ ➳ አድርግ፣ አታድርግ
- ትእዛዝከ ➳ ትእዛዝኽ
- ትእዛዘከ ➳ ትእዛዝኽን (ተሳቢ)

- **ዘአፍቀርኩ**

- አፍቀረ ➳ ወደደ
- አፍቀርኩ ➳ ወደድኹ
- ዘአፍቀርኩ ➳ የወደድኹ
- ጥቀ ➳ በጣም፣ እጅግ
- ዘአፍቀርኩ ጥቀ ➳ እጅግ የወደድኹ

- **ወአነሥእ**

- ነሥአ ➳ ያዘ፣ አነሣ፣ ተሸከመ
- ነሣእኩ ➳ አነሣኹ

- እነሥእ ➳ አነሣለኹ
- እንሣእ ➳ አነሣ ዘንድ
- እንሣእ ➳ ላንሣ
- **እደውየ**
- ዕድ ➳ ወንድ፣ ተባዕት
- እድ ➳ እጅ
- እደው ➳ እጆች
- እደውየ ➳ እጆቼ፣ እጆቼን (ለገቢርም ለተገብሮ ይኾናል)
- አነሥእ እደውየ ➳ እጆቼን አነሣለኹ

ከላይ የተጠቀሱት በሙሉ ከመዝገበ ቃላት ፍቺ አንጻር ሲኾን መጀመሪያ ቃላት የተቀመጠው የግእዙም ኾነ የአማርኛው ንባብ በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ

ሲሾን አንድ ቃል እንደአገባቡ የተለያየ ፍቺ ሊኖረው እንደሚችል እንረዳለን።

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን።🌻

በመምህር ግዛቸው ደጀኑ

□—🌷—□ **ነሐሴ ፩** □—🌷—□

ነሐሴ ፪

ምስባክ ዘነሐሴ ፪ ።

▪ *መዝ ፸፬፥ ፲፩-፲፫*

ወይወሰዱ ለንጉሥ ደናግለ ድኅሬሃ፥

ወቢጻሂ ይወሰዱ ለከ።

ወይወሰድዎን በትፍሥሕት ወበሐሤት፤

▪ መዝ ፸፬ (፸፭) ፥ ፲፩-፲፫

በኋላዋ ደናግሉን ለንጉሥ ይወስዳሉ፥

ባልንጀሮችዋንም ወደ አንተ ያቀርባሉ፤

በደስታና በሐሴት ይወስዱአቸዋል።

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር

- **ወይወስዱ**
  - ወሰደ → ወሰደ ፣ ይዘ ኼደ
  - ወሰዱ (ውእቶሙ) → ወሰዱ
  - ይወስዱ → ይወስዳሉ

- **ለንጉሥ**
  - ንጉሥ → የነግሠ ሳድስ ውስጠ ዘ ፣ የአቀባይ ባለቤት
  - ለ → አገባብ፣ ፍቺው → በቁም ቀሪ ፣

ሙያው → አቀባይ

  - ለንጉሥ → ለንጉሥ

- **ደናግለ**

◦ ደንገለ → ጠበቀ፣ ራሱን ከሴት አራቀ

◦ ድንግል (ዘመድ ዘር)→ ደናግል (ሲበዛ)

◦ ደናግለ → ድንግሎችን (ተሳቢ)

▪ **ድኅሬሃ**

◦ ድኅረ → ኋላ፣ ከኋላ

ድኅረ ደቂቅ አገባብ ሲኾን በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዘራል። ከዚኽ ውስጥ በይእቲ ሲዘረዘር ድኅሬሃ ነው።

◦ ድኅሬሃ → በኋላዋ፣ ከኋላዋ

▪ **ወቢጸሂ**

◦ ቤጸ → ለየ፣ መረጠ

◦ ቢጽ → ባልንጀራ፣ እኩያ፣ ወዳጅ

◦ ቢጸ → ባልንጀራዋ፣ ወዳጅዋ (የእሷ)

→ ባልንጀራዋን፥ ወዳጅዋን

→(ለገቢርም ለተገብሮም ይመቻል)

◦ ሂ → ም፣ ግን፣ ስንኳ ተብሎ ይፈታል።

◦ ወቢጸሂ → ባልንጀራዋንም

▪ **ለከ**

◦ ለከ → ለአንተ = ላንተ

→ መስተዋድዳዊ ተውላጠ ስም

▪ **ወይወሰድዎን**

◦ ወሰድዎ → እነሱ እሱን ወሰዱት።

ባለቤት ⇛ ውእቱ፣ ተሳቢ ⇛ ውእቱ

◦ ወሰድዎን → እነሱ (ውእቶሙ)

እነሱን (ውእቶን) ወሰዷቸው።

ባለቤት ➳ ውእቶሙ፣ ተሳቢ ➳ ውእቶን

◦ ይወስድዎን → ይወስዷቸዋል።

▪ **በትፍሥሕት**

◦ ተፈሥሐ → ተደሰተ፣ ደስ አለው

◦ ትፍሥሕት → ተድላ፣ ደስታ

→ ባዕድ ከምእላድ

◦ በ → አገባብ፣ ፍቺው → በቁም ቀሪ፣

ሙያው → ማድረጊያ

◦ ትፍሥሕት →የማድረጊያ ባለቤት

◦ በትፍሥሕት → በደስታ፣ በተድላ

- **ወበሐሤት**

◦ ተሐሠየ፣ ተሐሥየ → ተደሰተ፣ ዕሠይ አለ።

◦ ሐሤት → ፍጹም ደስታ፣ የልብ ተድላ

◦ በሐሤት → በፍጹም ደስታ፣ በተድላ

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን።🌻

□—🌷—□ **ነሐሴ ፪** □—🌷—□

ነሐሴ ፫

ምስባክ ዘነሐሴ ፫ ።

▪ *መዝ ፻፬ ፥ ፲፪ - ፲፫*

ወይሰግዳ ሎቱ አዋልደ ጢሮስ በአምጻ፥

ወለገጽኪ ይትማሐለሉ ሀሎሙ አሕዛብ ብዑላነ ምድር።

ኩሉ ክብራ ለወለተ ንጉሥ ሐሴቦን።

▪ መዝ ፻፬ ። (፻፫) ፥ ፲፪ - ፲፫

የጢሮስ ሴቶች ልጆች እጅ መንሻን ይዘው ይሰግዱለታል።

የምድር ባለጠጎች አሕዛብ በፊትሽ ይማለላሉ።

ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ኹሉ ክብርዋ ነው፤

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር

- **ወይሰግዳ**
  - ሰገደ → ሰገደ
  - ሰገዳ → ሰገዱ (ውእቶን)
  - ወይሰግዳ ← ይሰግዳሉ
  - ይስግዳ ← ይሰግዱ ዘንድ
  - ይስግዳ ← ይሰገዱ
- **ሎቱ**
  - ሎቱ → ለእሱ

    → መስተዋድዳዊ ተውላጠ ስም
  - ወይሰግዳ ሎቱ → ይሰግዱለታል።
- **አዋልደ**
  - ወልድ → ውሉድ

◦ ወለት → አዋልት። መሸን ሲገባው አዋልድ → ሴት ልጆች ይላል።

አዋልድ የሚለው ቃል ጢሮስ ከሚለው ጋራ ለመናበብ

ድ ➵ ደ መቀየር አለበት።

◦ አዋልደ ጢሮስ → የጢሮስ ልጆች

▪ **በአምኃ**

◦ አምጎ → እጅ ነሣ፣ እጅ መንሻ ሰጠ

◦ አምኃ → እጅ መንሻ፣ በረከት

◦ በ በደቂቅ አገባብነቷ በብዙ መንገድ የምትፈታ ሲሾን በዚኽ አገባቧ

◦ በአምኃ → እጅ መንሻን ይዘው ተብሎ መፈታቱን እናስተውላለን።

▪ **ወለገጽኪ**

◦ ገጽ → ፊት

ገጽኪ → ፊትሽ

◦ ለ በደቂቅ አገባብነቷ በብዙ መንገድ የምትፈታ ሲኾን በቁም ቀሪ ፣ እንዲኹም በ ተብላ ትፈታለች።

ለገጽኪ → በፊትሽ የተባለው ለዚኽ ነው።

▪ **ይትማሐለሉ**

◦ መሐለ → ማለ

ተማሐለ → ተማማለ፣ ተፈጣጠመ

ተማሕለለ → ተማለለ፣ ለመነ፣ ማለደ

ይትማሐለሉ → ይማለላሉ፣ ይለምናሉ።

▪ **ኵሎሙ**

◦ ኵሎሙ → ኹሉም

▪ **አሕዛብ**

◦ ሕዝብ → ወገን፣ ነገድ፣ የተሰበሰበ ብዙ ሰው

◦ ሕዝብ ሲበዛ አሕዛብ

▪ **ብዑላነ ምድር**

◦ ብዕለ →ከበረ፣ ባለጠጋ ኾነ

◦ ብዑል → የከበረ፣ ባለጠጋ (ሳድስ ቅጽል)

ብዑላን → ሳድስ ቅጽል (በብዙ)

ብዑላን የሚለው ከምድር የሚናበበው ን ወደ ነ ተቀይሮ ነው።

▣ ብዑላነ ምድር → የምድር ባለጠጎች

▪ **ኵሉ**

◦ ኵሉ → ኹሉ

▪ ክብራ

◦ ከብረ → ከበረ

ክብር → ዘመድ ዘር

ክብር የሚለው በይእቲ ሲዘረዘር ክብራ →ክብሯ

▪ **ለወለተ ንጉሠ ሐሴቦን።**

ወለት ንጉሥ ሐሴቦን

ሦስቱን ቃል ለማናበብ

ወለተ ንጉሥ ሐሴቦን

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን።🌻



▬▬❀▬▬ ነሐሴ ፬ ▬▬❀▬▬

ምስባክ ዘነሐሴ ፬ ።

▪ መዝ ፷፥ ፭-፪

እግዚኦ በኀይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ፥

ወበዙኀ ይትሐሠይ በአድኅኖትከ።

ፍትወተ ነፍሱ ወሀብኮ።

▪ መዝ ፷። (፷፩) ፥ ፭ - ፪

አቤቱ ፡ በኃይልኽ ፡ ንጉሥ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤

በማዳንኽ ፡ እጅግ ፡ ሐሤትን ፡ ያደርጋል ፤

የልቡን ፡ ፈቃድ ፡ ሰጠኸው ።

ከግእዝ ሰዋስው አንጻር

- **እግዚአ**
  - እግዚአ ➸ አቤቱ ፣ ጌታ ሆይ
- **በጎይልከ**

◦ ጌለ = ጎየለ → ጮኸ፣ ድረሱልኝ አለ

ጌለ→የጎይል→ይጒል→ይጒል (ቀተ)

◦ ጎየለ → በረታ፣ ዐየለ፣ ጎይለኛ ኾነ

ይጌይል→ የጎይል→የጎይል (ቀደ)

◦ ጎይል → ብርታት፣ ጉልበት፣ ጥንካሬ

◦ በጎይልከ → በጎይልኽ

በ → አገባብ፣ ፍቺው → በቁም ቀሪ = በ ፣ ሙያው → ማድረጊያ

ጎይል → የማድረጊያ ባለቤት

ከ → ባለቤት አመልካች

- **ይትፈሣሕ**

◦ ተፈሥሐ → ተደሰተ፣ ደስ አለው

ይትፈሣሕ → ይደሰታል

ይትፈሣሕ → ይደሰት ዘንድ

ይትፈሣሕ → ይደሰት

- **ንጉሥ**

◦ ንጉሥ → ንጉሥ (ሳድስ ቅጽል)

- **ወብዙኅ**

◦ በዝኅ → በዛ፣ በረከተ

በዝኅ→ይበዝኅ→ይብዛኅ→ይብዛኅ

◦ ብዙኅ → የበዛ፣ ብዙ፣ እጅግ፣ ዐያሌ

→ ሳድስ ቅጽል

◦ ብዙኅ → ብዙ ኾኖ፣ በብዙ

ፍጡነ → በፍጥነት እንደምንለው

- **ይትሐሠይ**

ተሐሠየ፣ ተሐሥየ → ተደሰተ፣ ዕሠይ አለ።

ይትሐሠይ (ጥ) → ይደሰታል

ይትሐሠይ (ላ) → ይደሰት ዘንድ

ይትሐሠይ (ላ) → ይደሰት

- **በአድኅኖትከ**

◦ ድኅነ → ዳነ፣ ተረፈ

ይድኅን ← ይድኅን ← ይድኅን

◦ አድኅነ → አዳነ፣ ታደገ፣ ዐገዘ

አድጎኖ/ አድጎኖት → ማዳን (አርእስት)

አድጎኖትከ → ማዳንኽ

በአድጎኖትከ → በማዳንኽ

በ → በቁም ቀሪ

- **ፍትወተ**

◦ ፈተወ → ዐሰበ፣ ተመኘ፣ ከጀለ

ይፈቱ → ይፍቱ → ይፍቱ

ፍትወት → መመኘት፣ መውደድ፣ አምሮት

→ ሳቢ ዘር

- **ነፍሱ**

◦ ነፍሱ → ነፍሱ (የእሱ)

ፍትወት ከ ነፍሱ ጋራ ለመናበብ ት ➸ ተ ይቀየራል።

ፍትወተ ነፍሱ → የነፍሱን ፈቃድ፣ ሐሳብ

- **ወሀብኪ**
  - ወሀበ → ሰጠ
  - ወሀብኪ → ሰጠሽው (አንተ ለእሱ)
    → መሠሪ ግስ (ዝርዝር)

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን።🌻

▬▬🌼▬▬ ነሐሴ ፬ ▬▬🌼▬▬

▬▬❁▬▬ ነሐሴ ፭ ▬▬❁▬▬

ምስባክ ዘነሐሴ ፭



▪ *መዝ ፻፲፭ ፶፫- ፶፬*

ወትሠይመኒ ውሰተ ርእሰ ሕዝብ፡

ሕዝብ ዘኢየአምር ተቀንየ ሊተ።

ውሰተ ምስማዐ እዝን ተሰጥዉኒ፤



▪ መዝ ፻፲ ፡ (፻፲) ፡ ፶፫ - ፶፬

የአሕዛብም ፡ ራስ ፡ አድርገኽ ፡ ትሾመኛለኽ ፤

የማላውቀው ፡ ሕዝብም ፡ ይገዛልኛል ፤

በጆሮ ፡ሰምተው ፡ተገዙልኝ ።



ከግእዝ ሰዋስው አንጻር

- **ወትሠይመኒ**
  - ሢመ ➸ ሾመ
  - ሢምከኒ ➸ ሾምኸኝ (አንተ እኔን)

ትሠይመኒ ➸ ትሾመኛለኽ

ትሥይመኒ=ትሢመኒ ➸ትሾመኝ ዘንድ

ሢመኒ ➸ ሹመኝ።

- **ውስተ ርእሰ ሕዝብ፥**
  - ርእሰ ➸ ራስ ኾነ

ርእሰ ➸ ራስ

  - ውስተ በዋናነት ውስጥ ተብሎ ቢፈታም
  - ውስተ ርእሰ ሕዝብ ➸ በሕዝብ ላይ ራስ

- **ዘኢየአምር**
  - አእመረ ➵ አወቀ

የአምር ➵ ያውቃል

ኢየአምር ➵ አያውቅም

ዘኢየአምር ➵ የማያውቅ

- **ተቀንየ**
  - ተቀንየ ➵ ተገዛ
- **ሊተ**
  - ሊተ ➵ ለእኔ

➵ መስተዋድዳዊ ተውላጠ ስም

- **ምስማዐ**
  - ሰምዐ ➵ ሰማ፣ አደመጠ
  - ምስማዕ ➵ መስሚያ፣ ማሰሚያ
- **እዝን**

◦ እዝን ➵ ጆሮ

● **ተሰጥዒኒ**

◦ ተሰጥወ፣ ተሰጠወ ➵ ተሰጠ፣ ተሰጠው፣ ተቀበለ

ሌላ ትርጉሙ መለሰ፣ ተናገረ፣ ምላሽ ሰጠ፣ ታዘዘ፣ እሺ በጎ አለ።

◦ ተሰጥዒኒ ➵ እነሱ ለኔ ታዘዙኝ፣ ተገዙልኝ

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን።🌻

▬▬🌼▬▬ ነሐሴ ፭ ▬▬🌼▬▬

▬▬❁▬▬ ነሐሴ ፮ ▬▬❁▬▬

ምስባክ ዘነሐሴ ፮



▪ መዝ ፸፪ ፥ ፲-፲፩

ጽድቅ ምሉእ የማንከ ፤

ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን ፤

ወይትሐሠያ አዋልደ ይሁዳ ፤

በእንተ ፍትሕከ እግዚአ ።



▪ መዝ ፸፪ ፥ ፲-፲፩

ቀኝኽ ጽድቅን የተሞላች ናት ፥

አቤቱ ስለፍርድኽ የጽዮን ተራራ ደስ ይበለው፥

የአይሁድም ሴት ልጆች ሐሴት ያድርጉ።



ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር

- **ጽድቅ**
  - ጸድቀ ➵ እውነተኛ ኾነ
  - ጽድቅ ➵ በቁሙ ፣ እውነት
- **መልአ**
  - መልዐ ➵ እግር መንገድ ኼደ
  - መልአ ➵ መላ

ምሉእ ➵ የመላ (ሳድስ ቅጽል)

- **የማንከ**
  - የማን ➵ ቀኝ

የማንከ ➵ ቀኝኽ

- **ይትፌሥሓ**

◦ ተፈሥሐ ➵ ተደሰተ ፣ ደስ አለው

◦ ይትፌሣሕ ➵ ይደሰታል ፣ ደስ ይለዋል (ውእቱ)

ይትፌሥሓ ➵ ይደሰታሉ (ውእቶን)

● **አድባረ ጽዮን**

ደብር ➵ ተራራ

አድባር ➵ ተራሮች ፤

◦ (ተ)ጸወነ ➵ ተጠጋ

◦ ጽዮን ➵ በቁሙ ፣ መጠጊያ፣ መሸሸጊያ (ዘመድ ዘር)

አድባር ከጽዮን ጋር ለመናበብ ር ወደ ረ ይቀየራል ።

አድባረ ጽዮን ➵ የጽዮን ተራሮች

● ወይትሐሠያ

◦ ወ ➵ አገባብ ፤ ፍቹ ➵ ም

◦ ተሐሥየ ➵ ተደሰተ፣ ሐሤት አደረገ

◦ ተሐሥያ ➵ ተደሰቱ፣ ሐሤት አደረጉ (ውእቶን)

◦ ይትሐሠያ (ጥ) ➥ ይደሰታሉ፣ ሐሤት ያደርጋሉ

ይትሐሠያ (ላ) ➥ ይደሰቱ ዘንድ፣ ሐሤት ያደርጉ ዘንድ

ይትሐሠያ (ላ) ➥ ይደሰቱ ፣ ሐሤት ያድርጉ

● **አዋልደ ይሁዳ**

◦ ወልድ ➥ ወንድ ልጅ

◦ አዋልድ ➥ በብዙ (ወንድ ልጆች)

◦ ወለት ➥ ሴት ልጅ

◦ አዋልት ➥ ሴት ልጆች (አዋልት መኾን ሲገባው አዋልድ ➥ ሴት ልጆች ይላል።

◦ ይሁዳ ➥ በቁሙ (የሰው ስም ፣ የነገድ ስም)

አዋልድ የሚለው ቃል ይሁዳ ከሚለው ጋራ ለመናበብ ድ ወደ ደ መቀየር አለበት።

◦ አዋልደ ይሁዳ ➥ የይሁዳ ሴት ልጆች

● **በእንተ ፍትሕከ**

◦ በእንተ ➷ ስለ ፣ ስለኾነ (አገባብ)

◦ ፈትሐ ➷ ፈረደ

◦ ፍትሕ ➷ በቁሙ ፣ ፍርድ (ዘመድ ዘር)

◦ ፍትሕከ ➷ ፍርድኽ

● **እግዚአ**

◦ እግዚአ ➷ አቤቱ ፣ ጌታ ሆይ

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን።🌻

ማለፊያ ደረጀ እምጇይ ዐውድ

□—🌺—□ **ነሐሴ ፮** □—🌺—□

▬▬❀▬▬ ነሐሴ ፭ ▬▬❀▬▬

ምስባክ ዘነሐሴ ፭



▪መዝ ፻፫፥ ፲፪

ብፁዕ ብእሲ ዘአንተ ገሠጽኮ እግዚኦ ።

ወዘመህርኮ ሕገከ።

ከመይትገኀሥ እመዋዕለ እኩያት።



▪መዝ ፻፫ ፥ ፲፪

አቤቱ አንተ የገሠጽኸው ሰው ምስጉን ነው ፤

ሕግኽንም ያስተማርኸው ፤

ከክፉዎች ዘመናት ይርቅ ዘንድ ።



ከግእዝ ቋንቋ ሰዋሰው አንጻር

- **ብፁዕ**
  - በፅዐ ➵ ተሳለ
  - ብፁዕ ➵ በቁሙ፣ የተሳለ፣ ምስጉን፣ ልዩ (ሳድስ ቅጽል)
- **ብእሲ**
  - ብእሲ ➵ ሰው
- **ዘአንተ ገሠጽኮ**
  - ዘ ➵ የ (ግልጸ ዘ ቅጽል)
  - አንተ ➵ አንተ (ተውላጠ ስም)
  - ገሠጸ ➵ ገሠጸ ፣ ተቈጣ
  - ገሠጽኮ ➵ ገሠጽኸው ፣ ተቈጣኸው (መሠሪ ግስ)

    ባለቤት ➵ አንተ

    ተሳቢ ➵ እሱን

ዘአንተ ገሠጽኮ ➵ አንተ የገሠጽኸው

- **እግዚአ**

◦ እግዚአ ➵ አቤቱ

- **ወዘመህርኮ**

◦ ወ ➵ አገባብ ፤ ፍቹ ➵ ም ፤ ሙያው ➵ መስተጻምር ።

ኹለት ማሰሪያ አንቀጽ ስላለ ለማያያዝ ወ እንጠቀማለን።

◦ ዘ ➵ የ

◦ መህረ ➵ አስተማረ

◦ መህርኮ ➵ አስተማርኸው (አንተ ፣ እሱን)

ባለቤት ➵ አንተ

ተሳቢ ➵ ውእቱ

ወዘመህርኮ ➵ ያስተማርኸው

- **ሕገከ**

◦ ሐገገ ➵ ሕግ ሠራ ፣ ወሰነ

◦ ሕግ ➵ ሕግ (ዘመድ ዘር)

◦ ሕግከ ➵ ሕግኽ

ሕግከ የሚለውን ተሳቢ ለማድረግ ከባለቤት አመልካች በፊት ሳድስ የነበረችው ግ ወደ ግእዝ ገ ትቀየራለች ።

ሕገከ ➵ ሕግኽን

- **ከመ ይትገኀሥ**

◦ ገኀሠ/ግኀሠ ➵ ራቀ ፣ ወገደ ፣ ለየ

◦ ተግሕሠ ➵ ራቀ ፣ ተለየ ፣ ተወገደ (ተገብሮ ግስ)

◦ ይትገሐሥ ➵ ይርቃል ፣ ይወገዳል ፣ ይለያል

◦ ይትገሐሥ ➵ ይርቅ ዘንድ ፣ ይወገድ ዘንድ

◦ ይትገሐሥ ➵ ይራቅ ፣ ይወገድ

ከመ ይትገሐሥ ➵ እንዲርቅ፣ ይርቅ ዘንድ፣ ይወገድ ዘንድ

- **እመዋዕለ እኩያት**

◦ እም ➵ ከ

◦ ውዕለ ➵ ዋለ

◦ መዋዕል ➵ ጊዜ ፣ ዘመን

◦ አከየ ➵ ከፋ

◦ እኩይ ➵ የከፋ ፣ ክፉ (ሳድስ ቅጽል)

◦ እኪት ➵ የከፋች ፣ ክፉ

◦ እኩያት ➵ የከፉ ፣ ክፉዎች (ለብዙ አንስት)

መዋዕል ከእኩያት ለመናበብ ል ወደ ለ ይቀየራል።

◦ እመዋዕለ እኩያት ➵ ከክፉዎች ዘመን

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን።

ነሐሴ ፳

ምስባክ ዘነሐሴ ፳ ።

▪ መዝ ፷፫ -፬

ወድቀት እሳት ወኢርኢክዋ ለፀሐይ ፤

ዘእንበለ ይትዐወቅ ሥክከሙ ሕለተ ኮነ ፤

ከመ ሕያዋን በመዐቱ ይውኀጠክሙ ።

▪ መዝ ፷፫ - ፬

እሳት ወደቀች ፤ ፀሐይንም አላየኋትም ፤

እሾኻችኹ ሳይታወቅ በትር ኾነ ፤

ሕያዋን ሳላችኹ በቁጣው ይውጣችኋል ።

ከግእዝ ሰዋስው አንጻር

- **ወድቀት**

◦ ወድቀ → ወደቀ (ውእቱ)

◦ ወድቀት → ወደቀች (ይእቲ)

- **እሳት**

◦ እሳት → በቁሙ [በቁሙ ማለት ዐማርኛው እና ግእዙ ተመሳሳይ ነው ለማለት ነው።]

- **ወኢርኢክዋ**

◦ ርእየ → አየ

° ርኢኩ → አየኹ [የዋህ ርባታ]

◦ ርኢክዋ → አየኳት (እኔ እሷን) [ዝርዝር ርባታ]

ባለቤት → አነ

ተሳቢ → ይእቲ

◦ ኢ → አፍራሽ

◦ ወኢርኢክዋ → አላየኋትም

● **ለፀሐይ**

◦ ለ → ን ፤ ሙያዋ → ተጠቃሽ

◦ በዝርዝር ርባታ ጊዜ የ ለ ሙያ ተጠቃሽ ናት።

◦ ፀሐይ → በቁሙ

◦ ለፀሐይ → ፀሐይን

● **ዘእንበለ**

◦ ዘ → እንበለ'ን አዳማቂ [ዘ ቢኖርም ባይኖርም ትርጉሙ አይለያይም ማለት ነው።]

◦ እንበለ → ሳ

● **ይትዐወቅ**

◦ ዖቀ (ዐወቀ) → ዐወቀ

◦ ተዐውቀ → ታወቀ

◦ ይትዐወቅ → ይታወቃል

◦ ዘእንበለ ይትዐወቅ → ሳይታወቅ

● **ሦክክሙ**

◦ ሦክ → እሾኽ

◦ ሦክክሙ → እሾኻችኹ [አንትሙ የስም ዝርዝር]

● **ሕለተ ኮነ**

◦ ሐለተ → መለመለ

◦ ሕለት → ዘንግ ፣ በትር (ዘመድ ዘር)

◦ ሕለተ → በትርን

አንድን በሳድስ የሚጨርስ ስም ወደ ተሳቢነት ለመቀየር የመድረሻ ፊደሉን ወደ ግእዝ እንለውጠዋለን። [ሕለት→ሕለተ]

◦ ኮነ → ኾነ

◦ ሕለተ ኮነ → በትርን ኾነ

● **ከመ ሕያዋን**

◦ ከመ → እንደ

◦ ሐይወ → ኖረ ፣ ሕያው ኾነ

◦ ሕያው → በቁሙ (ሳድስ ውስጠ ዘ)

◦ ሕያዋን → በብዙ

● **በመዐቱ**

◦ በ → አገባብ ፤ ፍቹ → በቁም ቀሪ ፤ ሙያው → ማድረጊያ

◦ መአተ → በዛ

◦ መአት → እጅግ ብዙ

◦ በመአቱ → በብዛቱ

◦ መዐተ → ተቆጣ ፣ ተበሳጨ

◦ መዐት → ቁጣ ፣ ብስጭት (ዘመድ ዘር)

◦ መዐቱ → ቁጣው [የውእቱ ርባታ]

● **ይውኅጠክሙ**

◦ ውኅጠ → ዋጠ [ሥርወ ግስ]

° ይውኅጥ → ይውጣል [ደቂቅ ርባታ]

◦ ይውኅጠክሙ → ይውጣችኋል (እሱ እናንተን) [ዝርዝር ርባታ]

ባለቤት → ውእቱ

ተሳቢ → አንትሙ

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን አሜን!🌻

ኅብስት ዘ. እምኵይ ዐውድ

▬▬🌼▬▬ ነሐሴ ፳ ▬▬🌼▬▬

ነሐሴ ፬

ምስባክ ዘነሐሴ ፬

▪ *መዝ ፹ ፥ ፬ - ፲*

ወትቀውም ንግሥት በየማንከ ፤

በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወጉብርት ፥

ሰምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምዒ እዝንኪ ።

▪ መዝ ፹ ፥ ፬ - ፲

በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ፤

ንግሥቲቱ በቀኝኽ ትቆማለች ፤

ልጄ ሆይ ስሚ እዪ ጕሮሽንም አዘንብዪ ።

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር

- **ወትቀውም**
  - ቆመ → ቆመ
  - ቆመት → ቆመች
  - ትቀውም → ትቆማለች
  - ትቁም → ትቆም ዘንድ
  - ትቁም → ትቁም
- **ንግሥት**
  - ነግሠ → ነገሠ
  - ነግሠት → ነገሠች
  - ንግሥት → በቁሙ ፣ የነገሠች (ሳድስ ውስጠ ዘ ቅጽል)

- **በየማንከ**

◦ በ → አገባብ ፣ ፍቺው → በቁም ቀሪ ፣ ሙያው → ማድረጊያ

◦ የማን → ቀኝ

◦ ከ → አመልካች ቅጽል

◦ በየማንከ → በቀኝኽ

- **በአልባሰ ወርቅ**

◦ በ → በ

◦ ለብሰ → ለበሰ

◦ ልብስ → በቁሙ (ዘመድ ዘር) ሲበዛ

◦ አልባስ → ልብሶች

◦ ወርቅ → በቁሙ

አልባስ ከወርቅ ጋር ለመናበብ ስ ወደ ሰ ይቀየራል ።

◦ በአልባሰ ወርቅ → በወርቅ ልብሶች

- **ዐጽፍት**
  - ዐጸፈ → ለበሰ ፣ ተጐናጸፈ
  - ዑጹፍ → የለበሰ ፣ የተጎናጸፈ (ሳድስ ውስጠ ዘ ቅጽል)
  - ዑጽፍት → የለበሰች ፣ የተጐናጸፈች (ለብሳ፣ ተጐናጽፋ)
- **ወኅብርት**
  - ወ → እና
  - ኀብረ → አንድ ኾነ
  - ኅብርት → አንድ የኾነች
  - ኖበረ → ሸለመ
  - ኅብርት → የተሸለመች (ሳድስ ውስጠ ዘ ቅጽል)
- **ስምዒ**
  - ሰምዐ → ሰማ

- ሰማዕኪ → ሰማሽ
- ትሰምዒ → ትሰሚያለሽ
- ትሰምዒ → ትሰሚ ዘንድ
- ሰምዒ → ሰሚ

- **ወለትየ**
  - ወለት → ሴት ልጅ
  - ወለትየ → ሴት ልጄ
- **ወርእዩ**
  - ወ → ም
  - ርእየ → አየ
  - ርኢኪ → አየሽ
  - ትሬእዩ → ታያለሽ
  - ትርእዩ → ታዪ ዘንድ

◦ ርእዩ → እዩ

● **ወአጽምዒ**

◦ ወ → ም

◦ አጽምዐ → አደመጠ (ሥርወ ግስ)

◦ አጽማዕኪ → አደመጥሽ (የዋህ ርባታ)

◦ ታጸምዒ → ታደምጫለሽ (ትንቢት)

◦ ታጽምዒ → ታደምጪ ዘንድ (ዘንድ)

◦ አጽምዒ → አድምጪ (ትእዛዝ)

◦ ወአጽምዒ → አድምጬም

● **እዝነኪ**

◦ እዝን → ጉሮ

◦ እዝንኪ → ጉሮሽ

ተሳቢ ለመኾን ከባለቤት አመልካች በፊት ያለው ሳድስ ፊደል ን ወደ ግእዝ ፊደል ነ መቀየር አለበት።

◦ እዝነኪ → ጉሮሽን

🌻እመብርሃን ጉሮዋን ሰጥታን ጨኸታችንን ሰምታን ካለንበት ኹሉ ችግር ታውጣን አሜን! 🌻

ማርታ አብርሃም እምይይ ዐውድ

▬▬🌼▬▬ ነሐሴ ፱ ▬▬🌼▬▬

ነሐሴ ፲

ምስባክ ዘነሐሴ ፲

▪ *መዝ ፸፫ ፥ ፪*

ተዘከር ማኅበረከ ዘአቅደምከ ፈጠረ ፤

ወአድኅንከ በትረ ርስትከ ፤

ደብረ ጽዮን ዘኀደርከ ውስቴታ።።

▪ መዝ ፸፫ ፥ ፪

አስቀድመኽ የፈጠርኸውን ማኅበርኽን ዐስብ፤

የርስትኽንም በትር አዳንኽ ፤

በውስጧ ያደርኽ የጽዮንን ተራራ ።።

ከግእዝ ሰዋስው አንጻር

- **ተዘከር**

◦ (ተ)ዘከረ → ዐሰበ ፣ ስም ጠራ

◦ ተዘከርከ → ዐሰብኽ

◦ ትዜከር → ታስባለኽ (ተ ን ውጠው ከሚያስቀሩ ቀለማት አንዱ ዘ ነው ። ስለዚህ በእርባታ ጊዜ ተ ይጎረዳል)

◦ ትዘከር → ታስብ ዘንድ

◦ ተዘከር → ዐስብ

◦ **ማኅበረከ**

◦ ኅብረ → አንድ ኾነ

◦ ማኅበር → በቁሙ ፣ አንድነት ስብስብ (ባዕድ ዘር)

◦ ማኅበርከ → ማኅበርኽ

ተሳቢ ለመኾን ከባለቤት አመልካች በፊት ያለው ር ወደ ረ ይቀየራል ።

◦ ማኅበረከ → ማኅበርኽን ፣ ጉባኤኽን ፣ አንድነትኽን

- **ዘአቅደምከ ፈጢረ**

◦ ዘ → የ (ግልጸ ዘ)

◦ ቀደመ → ቀደመ

◦ አቅደመ → አስቀደመ (አግባሪ ዐምድ)

◦ አቅደምከ → አስቀደምኽ

◦ ታቀድም → ታስቀድማለኽ

◦ ታቅድም → ታስቀድም ዘንድ

◦ አቅድም → አስቀድም

◦ ፈጠረ → ፈጠረ

◦ ፈጢሮ → ፈጥሮ (ቦዝ አንቀጽ)

◦ ፈጢረከ → ፈጥረኽ

◦ ፈጢረ → የፈጠርኸውን

● ዘአቅደምከ ፈጢረ → አስቀድመኽ የፈጠርኸውን

● **ወአድኅንከ**

◦ ወ → አገባብ ፣ ፍኾ → ም

◦ ድኅነ → ዳነ

◦ አድኅነ → አዳነ ፣ ተቤዠ (አግባሪ ግስ ፣ ተደራጊ ዐምድ)

◦ አድኅንከ → አዳንኽ

● **በትረ ርስትከ**

◦ በትር → በትር ፣ ዘንግ (ተሳቢ ለማድረግ በትረ ይኾናል)

◦ ርስት → ርስት፣ የሚወረስ ሀብት

◦ ርስትከ → ርስትኽ (ከ ባለቤት አመልካች

◦ በትረ ርስትከ → የርስትኽን በትር

● ደብረ ጽዮን

◦ ደብር → ተራራ

◦ ጽዮን → በቁሙ ፣ መጠጊያ መሸሸጊያ (ዘመድ ዘር)

◦ ደብረ ጽዮን → የጽዮን ተራራ

● ዘኀደርከ ውስቴታ

◦ ዘ → አገባብ ፤ ፍች → የ

◦ ኀደረ → ዐደረ

◦ ኀደርከ → ዐደርኽ

◦ ውስተ → (በ) ውስጥ (አገባብ)

◦ ውስቴቱ → (በ) ውስጡ (የውእቱ ርባታ)

- ውስቴታ → (በ) ውስጧ (የይእቲ ርባታ)
- ዘጎደርከ ውስቴታ → በውስጧ ፣ በርሷ ያደርኸባት

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤቷና በረከቷ አይለየን።🌻

ሳሙኤል ጎ/ሚካኤል እምፒይ ዐውደ

▬▬🌼▬▬ ነሐሴ ፲ ▬▬🌼▬▬

ነሐሴ ፲፪

ምስባክ ዘነሐሴ ፲፪ ።

▪መዝ ፸፬፥፲፮ - ፲፰

ሀየንተ ፡ አበውኪ ፡ ተወልዱ ፡ ለኪ ፡ ደቂቅ፤

ወትሠይሚዮሙ ፡ መላእክተ ፡ ለኩሉ ፡ ምድር፤

ወይዘክሩ ፡ ሰመኪ ፡ በኩሉ ፡ ትዉልደ ፡ ትዉልድ።

▪መዝ ፸፬፥፲፮ - ፲፰

በአባቶችሽ ፋንታ ልጆች ተወለዱልሽ ፤

በምድር ኹሉ ላይ ገዢዎች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ ፤

ለልጅ ልጅ ኹሉ ስምሽን ያሳስባሉ ።

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር ፦

- **ህየንተ አበውኪ**
  - ህየንተ → ስለ ፣ ወደ ፣ ምትክ (ፋንታ)
  - አብ → አባት
  - አበው → አባቶች (ለብዙ ፣ ወንዶች)
  - አበውኪ ~ አባቶችሽ (የአንቲ ርባታ)
  - ህየንተ አበውኪ → ስለ አባቶችሽ ፋንታ ፣ በአባቶችሽ ፋንታ ፣ በአባቶችሽ ምትክ ፣ እንደ አባቶችሽ
- **ተወልዱ ለኪ ደቂቅ**
  - ወለደ → ወለደ
  - ተወልደ → ተወለደ (ተገባሪ ግስ ፣ ተደራጊ ዐምድ)
  - ተወልዱ → ተወለዱ

○ ለኪ → ላንቺ (መስተዋድዳዊ ተውላጠ ስም)

○ ደቀ → ልጅ ኾነ

○ ደቅ →ልጅ (ዘመድ ዘር)

○ ደቂቅ → ልጆች

○ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ → ልጆች ተወለዱልሽ

ለማን → ለአንቺ

ምን → ደቂቅ (ልጆች)

● **ወትሠይሚዮሙ**

○ ወ → ም

○ ሢመ (ሠየመ) → ሾመ (ሥርወ ግስ)

○ ሢምኪ → ሾምሽ (አንቲ የዋህ ርባታ)

○ ትሠይሚ → ትሾሚያለሽ (አንቲ ደቂቅ ርባታ)

○ትሠይሚዮሙ → ትሾሚያቸዋለሽ [አንቺ እነሱን] (ዝርዝር ፣ ዐቢይ ርባታ)

ባለቤት → አንቲ

ተሳቢ → ውእቶሙ

- **መላእክተ ለኩሉ ምድር**
  - መለከ → ገዛ ፣ ዐለቃ ኾነ
  - መልአክ → ገዢ ፣ ዐለቃ (ዘመድ ዘር)
  - መላእክት → ገዢዎች ፣ ዐለቆች
  - ለ → ለ (አገባብ)
  - ኩሉ → ኹሉ
  - መደረ → ጸና
  - ምድር → በቁሙ ፣ ጽኑዕ (ዘመድ ዘር)

መላእክት ተናባቢ ለመኾን ት ወደ ተ ይቀየራል።

- መላእክተ ለኩሉ ምድር → ለምድር ኹሉ ገዢዎች

- **ወይዘክሩ ስመኪ**
  - ወ → ም

○ ዘከረ → ዐሰበ ፣ ጠራ

ዘከረ በንባብ ጊዜ የቀደሰ ቤት ሲኾን በርባታ ጊዜ እንደ ቀተለም እንደ ቀደሰም የሚረባበት ጊዜ አለው ።

○ ዘከሩ → ዐሰቡ ፣ ጠሩ (ውእቶሙ ፣ የዋህ ርባታ)

○ ይዘክሩ → ያስባሉ ፣ ይጠራሉ (ደቂቅ ርባታ)

○ ሰየመ → ስም አወጣ ፣ ሰየመ

○ ስም → በቁሙ (ዘመድ ዘር)

○ ስምኪ → ስምሽ (የአንቲ ርባታ)

○ ስመኪ → ስምሽን (ተሳቢ)

○ ወይዘክሩ ስመኪ → ስምሽን ያስባሉ ፣ ያሳስባሉ ፣ ይጠራሉ ፣ ያስጠራሉ

● **በኵሉ ትውልደ ትውልድ**

○ በ → ብዙ ጊዜ በቁም ቀሪ እየኾነ የሚያገለግል ሲኾን አንዳንድ ጊዜ ለ እየተባለ ይተረጐማል ።

○ ኩሉ --- ኹሉ

- ትውልድ → ልጅ
- ትውልደ ትውልድ → የልጅ ልጅ
- ለኩሉ ትውልደ ትውልድ → ለልጅ ልጅ ኹሉ

🌻የእመቤታችን ፡ የቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ረድኤቷና ፡ በረከቷ ፡ ለኹላችን ፡ ሊኾን ፡ ይገባል። ለአገራችንም ፡ እንዲደርሰን ፡ የየዐቅማችንን ፡ ከመሥራት ፡ ጋር ፡ በጸሎት ፡ እንድንበረታ ፡ አባቶች ፡ ያዘዙንን ፡ አንዘንጋ። 🌻

🌻ሠናይ ሱባዔ ዘፍልሰታ ለማርያም ይኹን ለኩልነ ሕዝበ ክርስቲያን 🌻

ዘነሐሴ ፲፩ እስተዳላውያን

ደበበ አቡሐሰን እም፲፩ይ ዐውድ

ዓባይነሽ አክሊሉ እም፲፩ይ ዐውድ

ነሐሴ ፲፩

▬▬❁▬▬ ነሐሴ ፲፪ ▬▬❁▬▬

ምስባክ ዘነሐሴ ፲፪



▪ መዝ ፸፩ ፥ ፭ - ፱

እግዚኦ ኩነኔከ ሀቦ ለንጉሥ።

ጽድቀከኒ ለወልደ ንጉሥ።

ከመ ይኩንኖሙ ለሕዝብከ በጽድቅ።



▪ መዝ ፸፩ ፥ ፭ - ፱

አቤቱ ፍርድኽን ለንጉሥ ስጠው ፤

ጽድቅኽንም ለንጉሥ ልጅ ፤

ሕዝብን በጽድቅ ድሆችኽንም በፍርድ ይዳኝ ዘንድ ።



ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር:-

- **እግዚአ**
  - እግዚአ → አቤቱ ፣ ጌታ ሆይ
- **ኵነኔከ**
  - ኵነነ → ፈረደ
  - ኵነኔ → ፍርድ (ጥሬ ዘር)
  - ኵነኔከ → ፍርድኽ

በጎምስ የሚጨርሱ ስሞች ወደምንም ሳይቀየሩ ባሉበት ተሳቢ መኾን ይችላሉ ።

  - ኵነኔከ → ፍርድኽን
- **ሀቦ**
  - ወሀበ → ሰጠ

○ ወሀብኮ → ሰጠኸው [አንተ ፣ ለእሱ] (ዝርዝር ፣ ዐቢይ ርባታ)

ባለቤት → አንተ

ተሳቢ → ውእቱ

○ ትሁቦ → ትሰጠዋለኽ (ትንቢት)

○ ትሀቦ → ትሰጠው ዘንድ (ዘንድ)

○ ሀቦ → ስጠው (ትእዛዝ)

● **ለንጉሥ**

○ ለ → በቁም ቀሪ (አገባብ)

○ ነግሠ → ነገሠ (ሥርወ ግስ)

○ ንጉሥ → በቁሙ ፣ የነገሠ (ሳድስ ውስጠ ዘ ቅጽል)

○ ለንጉሥ → በቁሙ

● **ጽድቀከኒ**

○ ጸድቀ → እውነተኛ ኾነ

○ ጽድቅ → በቁሙ ፣ እውነት (ዘመድ ዘር)

○ ከ → ባለቤት አመልካች

○ ጽድቅከ → ጽድቅኽ ፣ እውነትኽ

በሳድስ የሚጨርሱ ስሞች ተሳቢ ለመኾን ከባለቤት አመልካች በፊት ያለውን ሳድስ ፊደል ቅ ወደ ግእዝ ፊደል ቀ ይቀይራሉ ።

○ ጽድቀከ → ጽድቅኽን ፣ እውነትኽን

○ ኒ → ም (አገባብ)

ይኽች ፊደል ንኡስ አገባብ ውስጥ የምትመደብ ስትኾን አንዳንድ ቦታ ላይም ጠቃሚ ፊደል እያሉ ይጠሯታል።

ፍቻም፦ ም ፣ ደግሞ ፣ እንኳን የሚል ትርጉም ትሰጠናለች።

ከአፍራሽ ግስ ጋር ስትገኝ ደግሞ ነገር ግን ወይም ግን ትኾናለች።

ሂ → በሥርዓተ ንባብ ጊዜ ደግሞ ትራሰ ቀለማት ተብለው ከሚመደቡት ውስጥ አንዷ ነች። በሰም መድረሻ ላይ እየገባች በተነሽ ፣ በተጣይ ፣ በሰያፍ እና በወዳቂ በአራቱም ንባብ ጊዜ ወድቀው እንዲነበቡ ታደርጋለች።

○ ጽድቀከኒ → ጽድቅኽንም ፣ እውነትኽንም

● **ለወልደ ንጉሥ**

○ ለ → በቁም ቀሪ (አገባብ)

○ ወልድ → ወንድ ልጅ

○ ንጉሥ → በቁሙ ፣ የነገሠ (ሳድስ ውስጠ ዘ ቅጽል)

ወልድ ከንጉሥ ጋር ለመናበብ ድ ወደ ደ ይቀየራር ።

○ ለወልደ ንጉሥ → ለንጉሥ ልጅ

● **ከመ ይኩንኖሙ**

ከመ → አገባብ ነው። ፍቹ ፦ እንደ፣ እንዲ፣ እንዳ፣ እንድ ስንደጋግመው ፦ ሲ፣ ሲ፣ ዘንድ ኹኖ እንደ ኹኔታው ይፈታል። እዚኽ ላይ ግን ዘንድ ይኾናል።

ሙያው = ማንጸሪያ

- **ይኰንኖሙ**
  - ኰነነ → ፈረደ
  - ይኴንን → ይፈርዳል
  - ይኰንን → ይፈርድ ዘንድ
  - ይኰንን → ይፍረድ
  - ይኴንኖሙ → ይፈርዳቸዋል ፣ ይፈርድላቸዋል
  - ይኰንኖሙ → ይፈርዳቸው ዘንድ ፣ ይፈርድላቸዋል ዘንድ
  - ይኰንኖሙ → ይፈርዳቸዋል ፣ ይፈርድላቸዋል ።
  - ከመ ይኰንኖሙ → ይፈርዳቸው ዘንድ ፣ ይፈርድላቸዋል ዘንድ
- **ለሕዝብከ**
  - ለ → ን (አገባብ ፣ ሙያዋ ተጠቃሽ)

○ ሕዝብ → ሕዝብ ፣ ወገን ፣ ነገድ ፣ የተሰበሰበ ብዙ ሰው ማለት ሲኾን ስመ ምእላድ ይባላል።

○ ከ → ባለቤት አመልካች

○ ለሕዝብከ → ሕዝብኽን

● **በጽድቅ**

○ በ → በቁም ቀሪ (አገባብ ፣ ሙያዋ → ማድረጊያ)

○ ጽድቅ → በቁሙ ፣ እውነት /ፍርድ

○ በጽድቅ → በቁሙ ፣ በእውነት

🌻ስብሐት ለእግዚአብሔር ልዑል!🌻

ሰውሳን ይመር እምጌይ ዐውድ

▬▬🌼▬▬ ነሐሴ ፲፪ ▬▬🌼▬▬

ነሐሴ ፲፫

ምስባክ ዘነሐሴ ፲፫

▪ መዝ ፹፫ ፥ ፲፪ – ፲፬

ታቦር ወአርሞንኤም በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ፥
ወይሴብሑ ለስምከ፥
መዝራዕትከ ምስለ ኀይል ።

▪ መዝ ፹፫ ፥ ፲፪ – ፲፬

ታቦር እና አርሞንኤም በስምኽ ደስ ይላቸዋል ፤
ስምኽንም ያመሰግናሉ ፤
ክንድኽ ከታይልኽ ጋር ነው።

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር ፦

- **ታቦር**
  - ታቦር → በቁሙ ፣ (ነባር ስም ፣ ስመ ደብር)
- **ወአርሞንኤም**
  - ወ → እና (አገባብ ፣ ሙያው → መስተጻምር)
  - አርሞንኤም → በቁሙ (ነባር ስም ፣ ስመ ደብር)
- **በስመ ዚአከ**
  - በ → በቁም ቀሪ (አገባብ ፣ ሙያው → ማድረጊያ)
  - ሰመየ → ስም አወጣ ፣ ሰየመ
  - ስም → በቀሙ (ዘመድ ዘር)
  - ዘ → የ (አገናዛቢ [ዘርፋዊ] ተውላጠ ስም)
  - ዚአሁ → የእሱ (የውእቱ ርባታ)

○ ዚኣከ → የአንተ (የአንተ ርባታ)

○ በስመ ዚኣከ → በአንተ ስም

● **ይትፌሥሑ**

○ ተፈሥሐ → ተደሰተ ፣ ደስ አለው

○ ተፈሥሑ → ተደሰቱ ፣ ደስ አላቸው (ውእቶሙ የዋህ ርባታ)

○ ይትፌሥሑ → ይደሰታሉ ፣ ደስ ይላቸዋል (ደቂቅ ርባታ ትንቢት አንቀጽ)

● **ወይሴብሑ ለስምከ**

○ ወ → ም

○ ሰብሐ → አመሰገነ

○ ሰብሑ → አመሰገኑ (የውእቶሙ የዋህ ርባታ)

○ ይሴብሑ → ያመሰግናሉ (የውእቶሙ ደቂቅ ርባታ)

○ ለ → ን (አገባብ ፣ ሙያው → ተጠቃሽ)

- ስምከ → ስምኽ
- ወይሴብሑ ለስምከ → ስምኽንም ያመሰግናሉ

- **መዝራዕትከ**
- መዝራዕት → ክንድ (ስመ አካል)
- መዝራዕትከ → ክንድኽ (የአንተ ርባታ)

- **ምስለ ጎይል**
- ምስለ → ከ... ጋር
- ጎየለ → በረታ
- ጎይል → በቁመ ፣ ብርታት (ዘመድ ዘር)
- ምስለ ጎይል → ከጎይል ጋር

ሙሴ በታቦር እመ ትሬኢ ደመና፤

ኢይምሰልከ እስኩ ዘይወርድ መና፤

ርደተ መና ጥዑም አምጣነ ተርፈ በሲና።

(ቅኔ ዘአምላኪየ ዘሊቃውንት)

ናሆም ግርማይ እምፀይ ዐውድ



▬▬❀▬▬ ነሐሴ ፲፬ ▬▬❀▬▬

ምስባክ ዘነሐሴ ፲፬ ።

▪መዝ ፻፫ ÷ ፬ - ፭

ዘአዘዝከ መድኃኒቶ ለያዕቆብ ፤

ብከ ንወግአሙ ለከሉሎም ፀርነ ፤

ወበሰምከ ናኃሥሮሙ ለእለ ቆሙ ላዕሌነ ።

▪መዝ ፻፫ ÷ ፬ - ፭

ለያዕቆብም መድኃኒትን እዘዝ ፤

ባንተ ጠላቶቻችንን እንወጋቸዋለን ፤

በስምኽም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን ።

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር ፦

- **ዘአዘዝከ**
  - ዘ ➳ የ
  - አዘዘ ➳ አዘዘ
  - ከ ➳ ባለቤት አመልካች
  - ዘአዘዝከ ➳ ያዘዝኽ
- **መድኃኒቶ**
  - መድኃኒት ➳ መድኃኒት (ባዕድ ከምእላድ ስም)
  - መድኀኒቱ ➳ መድኀኒቱ (የውእቱ ዝርዝር)
  - መድኃኒቶ ➳ መድኃኒቱን (በካእብ የሚጨርሱ ስሞች ተሳቢ ለመኾን የመጨረሻ ፊደላቸውን ወደ ሳብዕ ይቀይራሉ።)
- **ለያዕቆብ**

○ ለ ➳ በቁም ቀሪ (አገባብ ፤ ሙያው ➳ አቀባይ)

○ ያዕቆብ ➳ በቁሙ (ስመ ሰብእ)

ለያዕቆብ ➳ ለያዕቆብ

● ብከ

○ ቦቱ ➳ በእሱ (መስተዋድዳዊ ተውላጠ አስማት)

○ ብከ ➳ በአንተ

● ንወግአሙ

○ ወግአ ➳ ወጋ (ሥርወ ግስ)

○ ወጋእነ ➳ ወጋን (የንሕነ የዋህ ርባታ)

○ ንወግእ ➳ እንወጋለን (የንሕነ ደቂቅ ርባታ ፤ ትንቢት አንቀጽ)

○ ንወግአሙ ➳ እንወጋቸዋለን [እኛ ፤ እነሱን] (ዝርዝር ፤ ዐቢይ ርባታ)

ባለቤት ➳ ንሕነ

ተሳቢ ➳ ውእቶሙ

- **ለኩሎሙ**

○ ለ ➳ ን (አገባብ ፤ ሙያው ➳ ተጠቃሽ)

○ ኩሎሙ ➳ ኹሉም

○ ለኩሎሙ ➳ኹሉንም

- **ፀርነ**

○ ተፃረረ ➳ ተጣላ

○ ፀር ➳ ጠላት (ዘመድ ዘር)

○ ፀርነ ➳ ጠላታችን (የንሕነ ርባታ)

ለነጠላም ለብዙም ያገለግላል ።

○ ፀርነ ➳ ጠላቶቻችን

ጠላቶቻችንን ለማለት ፀረነ ቢል የተመቸ ነበር ።

- **ወበስምከ**

○ ወ ➳ ም (አገባብ ፤ ሙያው ➳ መስተጻምር)

○ በ ➳ በቁም ቀሪ (አገባብ ፤ ሙያው ➳ ማድረጊያ)

○ ስም ➳ ስም

○ ከ ➳ አመልካች ቅጽል

○ በስምከ ➳ በስምኽ

● **ናኀሥሮሙ**

○ ኀሠረ ➳ ጐሰቈለ፣ ተዋረደ

○ ኀሠርነ ➳ ጐሰቈልን ፣ ተዋረድን

○ ናኀሥር ➳ እናጐሳቍላለን ፣ እናዋርያለን (የንሕነ ደቂቅ ርባታ)

○ ናኀሥሮሙ ➳ እናጐሳቍላቸዋለን ፣ እናዋርዳቸዋለን [እኛ ፣ እነሱን] (ዝርዝር ፣ ዐቢይ ርባታ)

ባለቤት ➳ ንሕነ

ተሳቢ ➳ ውእቶሙ

- **ለእለ ቆሙ**

○ ለ ➳ ን (አገባብ ፣ ሙያው ➳ ተጠቃሽ)

ዘ ፣ እንተ እና እለ አገናዛቢ (ዘርፉዊ) ተውላጠ አስማት ሲኾኑ የ ተብለው ይተረጐማሉ።

ዘ ➳ ለነጠላም ፣ ለብዙም ያገለግላል ።

እንተ ➳ ለነጠላ ብቻ ያገለግላል ።

እለ ➳ ለብዙ ብቻ ያገለግላል ።

○ እለ ➳ የ

○ ቆመ ➳ ቆመ

○ ቆሙ ➳ ቆሙ

○ ለእለ ቆሙ ➳ የቆሙትን

- **ላዕሌነ**

ላዕለ ➳በ ... ላይ

ላዕሌነ ➳በላያችን ላይ ፣ በእኛ ላይ

▬▬❀▬▬ ነሐሴ ፲፪ ▬▬❀▬▬

ነሐሴ ፲፩

ምስባክ ዘነሐሴ ፲፩

▪መዝ ፻፫ ÷ ፬-፭

ውስተ ኵሉ ምድር ወፅአ ነገሮሙ ፤

ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ ፤

ወውስተ ፀሓይ ሤመ ጽላሎቶ ።።

▪መዝ ፻፫ ÷ ፬ - ፭

ድምፃቸው ወደ ምድር ኹሉ፤

ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ፤

በእነርሱም ውስጥ የፀሐይን ድንኳን አደረገ።

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር ፦

- **ውስተ ኲሉ ምድር**

○ ውስተ ➳ ውስጥ ፣ በ ... ውስጥ ተብሎ የሚፈታ ሲኾን እንደ አገባቡ ወደ ተብሎ ሊፈታ ይችላል ።

○ ኲሉ ➳ ኹሉ

○ መደረ ➳ ጸና

○ ምድር ➳ በቁሙ ፣ ጽኑዕ (ዘመድ ዘር)

○ ውስተ ኲሉ ምድር ➳ ወደ ምድር ኹሉ

- **ወፅአ**

○ ወፅአ ➳ ወጣ

- **ነገሮሙ**

○ ነገረ ➳ ነገረ ፣ ድምፅ አወጣ

○ ነገር ➳ በቁሙ ፣ ዜና (ድምፅ)

○ ነገሮሙ ➳ ነገራቸው ፣ ወሪያቸው ፣ ዜናቸው (ድምፃቸው) (የወእቶሙ ርባታ)

● **ወእስከ**

○ ወ ➳ ም (አገባብ ፣ ሙያው ➳ መስተጻምር)

○ እስከ ➳ በቁሙ (አገባብ ፤ ሙያው ➳ መገስገሻ)

● **አጽናፈ ዓለም**

○ ጸነፈ ➳ ዳርቻ ኸነ

○ ጽንፍ ➳ ዳርቻ ፣ ጫፍ ፣ ጥግ (ዘመድ ዘር)

○ አጽናፍ ➳ ዳርቻዎች ፣ ጫፎች

○ ዐለመ ➳ ፈጠረ

○ ዓለም ➳ በቁሙ (ዘመድ ዘር)

አጽናፍ ከዓለም ጋር ለመናበብ ፍ ወደ ፈ ይቀየራል ።

አጽናፈ ዓለም ➳ የዓለም ዳርቻዎች

- **በጽሐ**
  - በጽሐ ➳ ደረሰ (ግስ)
- **ነቢቦሙ**
  - ነበበ ➳ ተናገረ (ቃል አወጣ)
  - ነቢብ /ነቢቦት ➳ መናገር (ቃል ማውጣት)
  - ነቢቦሙ ➳ መናገራቸው (ቃላቸው)(የውእቶሙ ርባታ)
- **ወውስተ**
  - ወ ➳ ም (አገባብ)
  - ውስተ ➳ በ.... ውስጥ እንደ ኹኔታው በ...ላይ ተብሎ ሊፈታ ይችላል ።
- **ፀሓይ**
  - ፀሓይ ➳ ፀሓይ (ስመ ፍጥረት)
- **ሤመ**

○ ሤመ (ሠየመ) ➳ ሾመ

● ጽላሎቶ

○ ጸለለ ➳ ጋረደ ፣ ጥላ አደረገ

○ ጽላሎት ➳ ጥላ ፣ ቤት ፤ ድንኳን ፤ ማረፊያ ፤ ማደሪያ (ምእላድ ዘር)

ጽላሎቱ ➳ ድንኳኑ ፣ ጥላው (የውእቱ ርባታ)

በካእብ (ቱ) የሚጨርሱ ስሞች ተሳቢ ለመኾን ወደ ሳብዕ (ቶ) ይቀየራሉ ።

ጽላሎቶ ➳ ድንኳኑን ፣ ጥላውን

🌻የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በረከቷ በኹላችን ላይ ይደርብን አሜን!!!🌻

ሰላማዊት ሸዋዬ እምጅይ ዐውድ

▬▬❀▬▬ ነሐሴ ፲፮ ▬▬❀▬▬

ምስባክ ዘነሐሴ ፲፮

መዝ ፻፫፥ ፴-፴፭

ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል።

እግዚአብሔር ውሰተ ማእከላ ኢትትሀወክ፥

ወይረድኣ እግዚአብሔር ፍጽመ።

▪ መዝ ፻፫። (፻፯) ፥ ፴ - ፴፭

ልዑል ፡ ማደሪያውን ፡ ቀደሰ።

እግዚአብሔር ፡ በመካከልዋ ፡ ነው ፡ አትናወጥም ፥

እግዚአብሔርም ፡ ፈጥኖ ፡ ይረዳታል።

ከግእዝ ቋንቋ ሰዋስው አንጻር ፦

- ቀደሰ = አመሰገነ ፣ ባረከ ፣ አከበረ

  = ለየ፣ መረጠ፣ አገነነ፣ አነጻ

- ማኅደሮ

  - ኀደረ ➳ ዐደረ

  - ማኅደር ➳ ማደሪያ

    ➳ ባዕድ ዘር

  - ማኅደሩ ➳ የእሱ ማደሪያው

    ➳ የውእቱ ዝርዝር

ተሳቢ ለመኾን ሩ ወደ ሮ ይቀየራል ።

- ማኅደሮ ➳ ማደሪያውን

- ልዑል

- ለዐለ፣ ተልዕለ፣ ተለዐለ ➳ ከፍ ከፍ አለ
- ልዑል ➳ ሳድስ ቅጽል
- እግዚአብሔር ➳ እግዚአብሔር
- ውስተ ማእከላ
- ውስተ ➳ ውስጥ
- ማእከል ➳ መካከል

  ማእከላ ➳ መካከልዋ (የእሷ)

  ➳ የይእቲ ዝርዝር
- ኢትትሀወክ
- ሀወከ = ሆከ ➸ አወከ፥ አናወጠ
- ተሀውከ ➸ ታወከ፣ተናወጠ
- ተሀውከት ➸ ታወከች፣ ተናወጠች

  ትትሀወክ ➸ ትታወካለች፣ ትናወጣለች

ትትህወክ ➞ ትታወክ ዘንድ፣ ትናወጥ ዘንድ

ትትህወክ ➞ ትታወክ፣ ትናወጥ

ትንቢቱ ይጠብቃል ዘንዱና ትእዛዙ ላልቶ በመነበብ ይለያል።

ኢ ➞ አፍራሽ

ኢትትህወክ ➞ አትታወክም፣ አትናወጥም

- ወይረድኣ

◦ ረድአ ➞ ረዳ

ማን = እሱ ማንን ረዳ? አይታወቅም።

በመኾኑም ግሱ የዋህ ግስ፣ ርባታው ደግሞ የዋህ ርባታ ይባላል።

◦ ረድኣ ➞ ረዱ (ውእቶን) = የዋህ

ወይም

ረድኣ ➞ ረዳት (መሠሪ = ዝርዝር ግስ)

ማን (ባለቤት) = እሱ ፤

ማንን (ተሳቢ) = እሷን

ረድኣ ➸ ረዳት

ይረድኣ ➸ ይረዳታል

ይርድኣ ➸ ይረዳት ዘንድ

ይርድኣ ➸ ይርዳት

- እግዚአብሔር ➸ እግዚአብሔር
- ፍጽመ

ቅድስት ወብፅዕት

ስብሕት ወቡርክት

ክብርት ወልዕልት

ንጽሕት ወብርህት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

በረድኤትሽ፣ በጥበቃሽ አትለዪን።

ከዓመት ዓመት ከቀኑጥር አታጉድዪን።

ለአገራችን፣ ለዐሥራት አገርሽ ምሕረትን፣ ሰላምን ከተወዳጁ ልጅሽ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ለምኚልን። 

አሜን! አሜን! አሜን!

በመምህር ግዛቸው ደጀኑ



አነቃቅቶ ላስጀመረን አተጋግቶ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው!

ምስባክ ዘፍልሰታ ጸም

ነሐሴ ፳፻፲፭ ዓ/ም

ሙዳየ ግእዝ ቍጥር ፩



በመምህር ግዛቸው ደጀኑ አና በግእዝን በርቀት
ከ፩ኛ አሰከ ፲፩ኛ ዙር ተማሪዎች የተዘጋጀ ።